

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከሜይ 1-31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

# ከጁን 1-30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2026

አዲስ አበባ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


### 1.1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

በለፈዉ የሜይ ወር ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች፣ በተለይም በመጀመሪያዎቹ እና በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና ሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠሩት ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ መካከለኛ እና የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 49፣ አርባ ምንጭ 23፣ 45፣ ባህርዳር 21.9፣ አዋሳ 39.1፣ 30.9፣ ኮምቦልቻ 38.8፣ ደብረ ማርቆስ 29.4፣ 42.2፣ 29.8፣ 25.4፣ ቢሾፍቱ 23፣ 28.4፣ ጎዴ 45.4፣ 29.7፣ ጎሬ 25.8፣ 28.7፣ 34.3፣ 35.7፣ ጅማ 23.9፣ 45፣ 36.5፣ 21.9፣ መተሃራ 22፣ 27.6፣ ነቀምት 46፣ 32.4፣ 26.2፣ 57.7፣ 25.4፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 37፣ 21.8፣ አዴት 30፣ አደዋ 28፣ 30፣ አይራ 35.2፣ 23.2፣ 26.5፣ 20.2፣ ሀሮማያ 21.2፣ አለምከተማ 22.4፣ አማን 53.2፣ 23.5፣ 27.2፣ 27.6፣ አንገር ጉትን 23.2፣ 30.4. 25.8፣ አርጆ 20.4፣ 22.8፣ 34.6፣ 24.4. 20.8፣ አይከል 35.9፣ አርሲ ሮቤ 85.2፣ አሶሳ 24.7፣ 27.4፣ አጽቢ 23.1፣ 22.6፣ አይሻ 27፣ ባቲ 28፣ አምቦ 30.3፣ ብላቴ 53.8፣ 33.6፣ በደሌ 31.4፣ 54.8፣ 23.8፣ 21.4፣ 25.3፣ 58.8፣ 25፣ ቦሬ 76.8፣ 22.2፣ 20.5፣ 22.7፣28፣ ቡሂ 21.6፣ ቡለን 51.4፣ ቡርጂ 27.8፣ 53.8፣ ጨፋ 28.6፣ ቻግኒ 57.4፣ 20.2፣ 20.7 ጨዋቃ 23.2፣ 37፣ 20፣ 25.2፣ 20.2፣ 25፣ 30.5፣ 32፣ ጭራ 21.8፣ ጭፍራ 28.2፣ ዳንግላ 24.7፣ 33.7፣ 63፣34፣ 27.5፣ ደብረ ታቦር 22.7፣ 36.8፣ ደብረ ወርቅ 23.8፣ 21.8፣ ደምቢ ዶሎ 21.2፣ ዲላ 35.4፣ 33.5፣ 25.4፣ 20.4፣ ዶሎመና 20.5፣ 20.5፣ 30.1፣ ኢጃጂ 26.2፣ 21.5፣24.2፣ እነዋሬ 27፣ ፋኙዶ 23.6፣ 20.6፣ 68.8፣ ጋምቤላ 21.7፣ 27.2፣ ጋቲራ 23.1፣ 20.3፣ 21.1፣ ገለምሶ 22.5፣ 27.8፣52፣ 24.3፣ 21.2፣ ጊዳ አያና 21.3፣ 60.5፣ 59.2፣ 27.3፣ 24.3፣ ጊምቢ 32.4፣ 33.4፣ 26.7፣ ጊኒር 56፣ ጉንዶ መስቀል 26.7፣ ቡሌሆራ 22.5፣ 34.4፣ ሐረር 55፣ እምድብር 24.1፣ ጃራ 20.6፣ 22.4፣ ጅንካ 22.9፣ ቀቢሪ ዳር 28፣ ኮንሶ 33.2፣ ቁሉምሳ 65.2፣ 47.9፣ ላይብር 20.8፣ 25፣ 20፣ ሊሙገነት 37፣ 27.5፣ 29.5፣ 35.3፣ ማይጨዉ 27.5፣ ማጀቴ 26.9፣ ማጂ 23፣ 46፣ ማንኩሽ 31.6፣ 24.6፣ ሞጣ 26.6፣ 28፣ ማሻ 32.4፣ 30.6፣ መካነ ሰላም 20.7፣ ነጆ 26.1፣ 22.5፣ 23.7፣ 81.6፣ አዳማ 21፣ ንፋስ መዉጪያ 23.5፣ ኑራ ኤራ 22.1፣ ሳዉላ 39፣ 25.7፣ ሰኮሩ 20.8፣ 30.7፣ ሻምቡ 21.2፣ 33.5፣ ሽሬ 20.9፣ ሾላገበያ 21.9፣ ቴፒ 23.2፣ 28.2፣ 21.3፣ 36፣ 30.2፣ ተርጫ 36.4፣ 28.6፣ 34.8፣ ወራቤ 25.7፣

Ethiopian Meteorology Institute

29.9፣ 24.2፣ ወላይታ ሶዶ 31.5፣ 27፣ የትኖራ 24.3፣ 27.4. ያቤሎ 27.5፣ ባቱ 29.2፣ አዲስ አለም 29.1፣ አዲስ ዘመን 38.5፣ አቦሞሪንጋ 46.4፣ 26፣ አጋሮ 32.1፣ 29፣ 33.2፣ አቃቂ 55.9፣ አንጋጫ 28፣ አሸ. 28.4፣ 32፣ 24፣ 34.8፣ 24፣ ቡልቂ 20.4፣ 22.1፣ 20.8፣ 26.1፣ 26.5፣ ቢላምቢሎ 43.3፣ ደጋን 35.2፣ 20.4 ደብረ ሲና 29.6፣ ደዴሳ 37.9፣ ዲመካ 44.8፣ ጊዶሌ 29.4፣ 54.3፣ 21.2፣ ጊናገር 29.8፣ ጎሮ 51.1፣ ጉራ በቁሳ 25.5፣ ጎብዬ 29.5፣ 21.6፣ 25.5፣ ጉብቲ 30.4፣ 26.1፣ ሃራ 40.2፣ 20.6፣ ሃሮ 40.2፣ 20.2፣ 40.4፣ 20.2፣ 30.2፣ 40፣ 20፣ ሃርሺን 33.2. ካራሚሌ 40.9፣ ቀርሳ(ባሌ) 33.5፣ ቅዳሜ ገበያ 20.8፣ 32.7፣ 57.8፣ 21.4፣ ማርዬ 21.6፣ ምሆኒ 40፣ መርሳ 23.2፣ 25.6፣ 59.2፣መንደር13 32.6፣30.4፣ 32.2፣ 26.4፣ መንደር11 93.5፣ 33.5፣ 28.5፣ ሮቢት 86፣ 23.6፣ ሸንዲ 29.9፣ 21.5፣ 23.5፣ 36.5፣ ኦንገ 54.3፣ 38.5፣ ተልተሌ 35.5፣ ትንሹ ሜጢ 23.3፣ ወግዲ 20.4፣ 36.2 ዉልበርግ 29.3፣ 24.2፣ እንዲሁም ይርጋለም 22.2 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፈዉ የሜይ ወር በሰባ ስምንት (78) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡





ምስል 1: ከሜይ 1 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፈዉ የሜይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ምስራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ ሁሩጉድሩ ወለጋ ፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ቡኖ በድሌ፣ አርሲ አና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ከልል ዞኖቸ፣ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን ዞኖቸ፣ ከአማራ ክልል ባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ሃላባ፣ ሃዲያና ከንባታ ዞኖች ላይ ከ53-339 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ7-25 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ምስራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆረጉድሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ቡኖ በድሌ፣ አርሲ አና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖቸ፣ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን ዞኖቸ፣ ከአማራ ክልል ባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ሃላባ፣ ሃዲያና ከንባታ  በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር


## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### 1.2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 3/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የሜይ ወር በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የአፈር ዉስጥ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ተዘርተው ፍሬ በማፍራት እና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች እድገትና የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። እንዲሁም ከኤፕሪል ወር ጀምሮ ለተዘሩ እንደ ቦቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እድገትና ለመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወን በቂ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖር ያስቻለ ሲሆን በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳር እና ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4) ፡፡

### 1.3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 3/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሜይ ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ አይሻ፣ ኦጋዴን፣ ተከዜ እንዲሁም የአፋር ደናክል ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ እና በታችኛው አባይ ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድርን የውሃ መጠንን በማሻሻል ወደ ግድቦችኛ የውሃ መያዣዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከመጨመር አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በሌላ በኩል የተቀሩት የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛው ተከዜና የታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5) ።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል:: በጁን በመደበኛው ሁኔታ የተስፋፋ የዝናብ መጠንና ስርጭት የተሻለ መልክ የሚኖረው ከወሩ ከመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጀምሮ ነው። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-24 ቀናት ያህል ይዘንባል። ይሁንና በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ30-100ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ3-16 ቀናት ያህል ይዘንባል። ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁን የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

## 2.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ


በመደበኛው ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል፡፡

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

በመጪው የጁን ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎችም ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ደመናዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 3)፡፡ በአጠቃላይ በጁን ወር ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬ ዳዋ እና ሀረር፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ማዕከላዊ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግህምራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መከከለኛ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ የኢታንግ ልዩ ዞን እና ንዌር ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ እና ቡርጂ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል ፋፈን፣ ኤረር፣ ጃራር፣ ዞኖች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)። በጠቃላይ በሚቀጥለው የጁን ወር የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የሚገኘውን የዝናብ መጠንና ስርጭት በአግባቡ በመጠቀምና በማሳባሰብ በዚህ ወቅት የሚካሄደውን የግብርና እንቅስቃሴ ሥራዎችን ከባለሙያዎች ጋር በመመካከር ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

Ethiopian Meteorology Institute




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 1 እስከ 30/2026
የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከጁን 1 እስከ 30/2026
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጁን ወር በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችም ሆነ ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም የጓሮ አትክልቶችና ቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት ምቹ ሁኔታን የሚፈጠር በመሆኑ አርሶ አደሮች ተገቢ የሆኑ ግብዓቶችን በማካተት የእርሻ ሥራውን በተሟላ መልኩ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩ ግን አልፎ አልፎ በአንዳንድ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለወቅቱ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም በተወሰኑ ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሣዎች ላይ የውሃ መተኛትና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ስለሚችል ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ ማንጣፈፍ ቦዮችን መስራት፣ ተዳፋታማ እና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ

ማሳዎች ላይ ሰብሎች በጎርፍ እንዳይጠረጉ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በማዘጋጀት የቅድመ ጥንቃቄ ስራ ማከናወን ያስፈልጋል። በሌላም በኩል የሚጠበቀው እርጥበት ከሰኔ ወራት ጀምረው ለሚደርሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በመካከል በሚገኙ ደረቅ ቀናት የደረሱ የበልግ ሰብሎች መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ ኢንስቲትዩቱ ይጠቁማል።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው በጁን ወር በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ በላይኛው እና በመካከለኛው አዋሽ፣ በገናሌ ዳዋ፣ በዋቢ ሸበሌ እንዲሁም በኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ የሚኖረውን የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚያሻሽል ይጠበቃል። በአጠቃላይ በጁን ወር የሚጠበቀው የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ሁኔታ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ የውኃ ሀብት መሻሻልን የሚያመጣ ሲሆን፤ በአጠቃላይ በወሩ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን አዎንታዊ ጎን አጠናክሮ ለማስቀጠል እና አሉታዊ ክስተቶችን ለመቀነስ ቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ በመካከለኛው እና በታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ የኦጋዴን፣የአይሻ፣ የመረብ ጋሽና የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ፡፡

Ethiopian Meteorology Institute